*በእንቢልታ ጋዜጣ ላይ እንድጽፍ ስጠየቅ፣ አንድ ሃሳብ መጣልኝ። ጊዜው የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነውና ምናልባት ከሦስት ዓመት በኋላም ቢሆን ሃሳቤ ተቀባይነት ካገኘ በሚል፣ ከዚህ በፊት በ1997 ዓ.ም. በአንድ ጋዜጣ ላይ ጽፌው ለንባብ በቅቶ የነበረውን የ"ዕርቀ ሠላም" ሃሳብ ዛሬም ሳላፍል ብዬ ከተቀመጠበት አወጣሁ፣ ዕርቅና ሠላም ዛሬም ለሀገራችን ያስፈልጋታል! የአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ወር ሁለተኛ ቀን እንደመሆኑ ስለ ዕርቀ ሠላም ከዛሬው ልናስብበት ይገባል! መልካም ንባብ።*

***ሽመልስ ተክለጻድቅ (ዶ/ር)***

# ዕርቀ ሠላም

## ዕርቀ ሠላም ማን ይፈልጋል? ለምንስ ያስፈልገናል?

በተጣሉ ግለሰቦች፣ ወገኖች፣ ማኅበረሰቦች መካከል ከሠላም መለስተኛ በሆነ መልኩ በአሸናፊው ወገን ተጽዕኖና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መረጋጋት ሊፈጠር ይችላል። መረጋጋቱ ለረጅም ጊዜ ከቆየና የአሸናፊው እብሪት ከበረደ፣ ተሸናፊውም የደረሰበት የአካልም ሆነ የመንፈስ ቁስሉ ካገገመ ሠላሙ እየዳበረ መሄድ ይችላል።

ጥሉና መናቆሩ ከከረረ፣ ቅራኔው የርዕዮተ ዓለም እምነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ወይም ነው ብሎ ከታመነ፣ ግጭቱ ያስከተለውም ውጤት በሠፊው የነፍስ መጥፋትና የንብረት መውደም ካደረሰ፣ ግጭቱን ያስነሳው ግላዊም ሆነ ማኅበራዊ ቅራኔ ሳይፈታና አሸናፊና ተሸናፊውን ሳይለይ የግጭቱ ጊዜ ከተራዘመ፣ በተጣሉት ወገኖች መካከል ሠላም ሊወርድ የሚችለው በዕርቀ ሠላም መንገድ ብቻ ነው።

የየካቲቱ 1966 ዓ.ም. አብዮት በሀገራችንና በኅብረተሰባችን ውስጥ ያስነሳው ሁለገብ የሆነ ግጭትና ቀውስ እስካሁን አልበረደም። ህዝቡም ዘንድ የሚታይ ሥነልቦናዊ መናወጥ ፈጥሯል። የዚህ ቀጣይ ሁለገብ ቀውስ አመላካች ውጤቶች:-

- መጀመሪያው ላይ ለ17 ዓመታት በመደብ ትግል ስም የተካሄደው የእርስበርስ መጋደልና መቋሰል በብዙ ሺ ለሚቆጠሩ ዜጎች ሞትና አካለ ጎደሎ መሆን፣ በብዙ መቶ ሺ ለሚቆጠሩ ዜጎች ሀገራቸውን ጥለው ለመሰደድ፣ እንዲሁም ቁጥሩን ለመገመት የሚያቅት ሰው ከቀዬው ለመፈናቀል ምክንያት ሆኗል፤ በዚህ ወቅት "ፍራቻ" ህዝቡ ሥነልቡና ውስጥ ሥር ያዘ።
- ለብሔረሰቦች ነፃነት አስገኛለሁ በማለት በተካሄዱ የእርስበርስ ጦርነቶችም ያለቀው ሰው ቁጥርና የወደመው ንብረት እጅግ ብዙ ነው። አስከፊው ነገር ይህ ብቻም አይደለ፤ ወያኔ/ኢህአዴግ ሀገራችን ላይ የጎሣ ፌዴራሊያዊ አስተዳደር ሙከራ ሲያደርግ አሁን 17 ዓመት አልፎታል፤ ይህ ሙከራ በዜጎች (በተለያዩ ጎሣዎች) መካከል በጫረው ጸብ ብዙ ሰው እያለቀ፣ ንብረትም እየወደመ እንደገናም ብዙ ዜጎችም ከቀዬአቸው እየተፈናቀሉና ከሀገራቸውም እየተሰደዱ ነው። ሀገራችንም አንድነቷን ጠብቃ በነፃነት የመቆየቷ ዕድል ላይኖር

ይችላል ብለን እንሰጋለን። በህዝቡም ዘንድ ከደርግ ግዛት ዘመን የወረስነው ሁሉን ነገር የመፍራት ጠባይ ጋብ ሳይል የእርስ በርስ "የመጠራጠር/አለመተማመን" ሁኔታ ታከለበት።

- በዚህ ታሪካዊ ወቅት በጠመንጃ ኃይላቸው እገዛ የተፈራረቁት ሁለት መንግሥታት መሪዎች በእብሪትና በግብታዊነት አዲስ ኢትዮጵያና! አዲስ ኢትዮጵያዊ! እንፈጥራለን ብለው ደንፍተዋል። ነገር ግን ከታሪካችን፣ ባህላችንና ወጋችን የወረስነውን እሴቶች፣ የጋራ እምነቶችና ትዝታዎች (collective memory)፣ የአስተዳደርና የኑሮ ልምድ ከማፍረስ በቀር በቦታው የሚተካ፣ ህዝቡ የሚቀበለው አማራጭ እሴትና እምነት ማቅረብ በፍጹም አልቻሉም። ጭራሽ በጋራ የምናውቀው ሦንደቅ ዓላማችን ያኔ በቀይ ባንዲራ አሁን ደግሞ በብሔሮች መንግሥታት ባንዲራዎች ተከቦ እናየዋለን። ስንቶቻችን የአሁኑን ሀገራዊ መዝሙር ቃላቶችና ዜማ እናውቃለን? ባንድ ወቅት ያሁኑ ጠቅላይ ሚንስትር የሰንደቅ ዓላማችንን "ጨርቅነት" ሊያስተምሩንም ሙከራ ማድረጋቸውን በኀዘን እናስታውሳለን።
- ብዙ ዓይነት መሥዋዕትነት የተከፈለበትም የሶሻሊስት ተስፋና የብሔሮች እኩልነት ግብ ለመሪዎቹ የግዛት ዘመን ከማራዘም ውጭ ያስከተለው ማኅበራዊ ለውጥ አይታይም። በግልጽ ተገኙ የሚባሉትም እንደ የመሬት ሥሪት ሥር ነቀል ለውጥ፣ በጾታና በብሔረሰቦች መካከል ያሉት ወልጋዳ ግንኙነቶች በእኩልነት ላይ እንዲመሠረት የተደረሰው ስምምነት ገና አልሰከነም። ስለሆነም የለውጡን መልካም ገጽታ ማየት አስቸጋሪ ነው። በአንጻሩ በተከታታይ ከከፋ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ከወረስነው የፈሪነትና የተጠራጣሪነት ማኅበራዊ ሥነ ልቦናዊ በሽታ ሳንላቀቅ "ሀገራዊ ቅኝትና ስምምነት" እንድናጣ ምክንያት ሆኗል።
- በዚሁ ዘመን ሁለት የሀገራችን ርዕሰ ብሔሮችና ሁለት ጠቅላይ ሚንስትሮች ያለፍርድ ተገለዋል፤ አንድ ርዕሰ ብሔር በስደት ይኖራሉ፤ ያለፈውና ያሁኑ መንግሥት ጠቅላይ ሚንስትር የነበሩ ሁለት ግለሰቦችና ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከሌሎች ብዙ የፖለቲካ እስረኞች ጋር ከርቸሌ ወርደው ፍርድ ሳያገኙ እየማቀቁና የቤተ ዘመዶቻቸው ሸክም ሆነው ይኖራሉ።
- የሞቱት፣ አካለ ጎደሎ የሆኑት፣ የታሰሩት፣ የተፈናቀሉት፣ የተሰደዱት ዜጎች ሁሉ እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣ ልጅ፣ ዘመድ አዝማድና የሚወዷቸው ጓደኞች ስላሏቸው አሁን ባለነው ኢትዮጵያውያን መካከል በጣም ሰፊ የሆነ የሻከረ ስሜት መኖሩ ግልጽ ነው፤ ይህ ነው የሚባል ሀገራዊ ስምምነትም የለንም።

እንደኛ እንደዚህ ለብዙ ዓመታት ሁለገብ በሆነ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውስና ውጥረት ውስጥ ያለፉ በዓለማችን ያሉ ሀገሮች በጣም ጥቂት ናቸው። ብዙዎቹ፣ በላቲን አሜሪካና እስያ የሚገኙ ሀገሮች ይህን መሰል ቀውስና ውጥረት የተወጡት በዕርቀ ሠላም መንገድ ነው። በአህጉራችን የደቡብ አፍሪካ ዕርቀ ሠላም ተሞክሮ ከሁሉም የበለጠ የተሣካ አኩሪ ታሪክ ነው። እኛም ዕርቀ-ሠላም ሳናገኝ በጭፍን ብንጓዝ፣ መልካም መንግሥትና የተሻለ ፕሮግራም ይዞ በማሸነፍ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ቢቀርብም እንኳን ከተወሳሰቡ የችጋርና የኋላ ቀርነት ማነቆ ባፋጣኝ መላቀቅ አይቻለንም።

ስለሆነም "በሀገራችን የሚመሠረተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማይናወጥ ጠንካራ መሠረት ላይ መቆም ካለበት የእስካሁኑ የጥላቻ፣ የበቀልና ያለመተማመን ምዕራፍ ተዘግቶ ለተከታታይ ትውልድ የሚዘልቅ አዲስ ምዕራፍ መከፈት ይኖርበታል። በመሆኑም እያንዳንዳችን ከራሣችን፣ ህዝብ ከህዝብ፣ መንግሥት ከህዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር ለመግባባት የሚችሉበት ብሔራዊ ዕርቀ ሠላም ከሁሉ በፊት መቅደም አለበት።

## ዕርቀ ሠላም እንዴት ይገኛል?

ብሔራዊ ዕርቀ ሠላም በተለያዩ መንገዶች ሊደረግ ይቻላል፣ አንዱ መንገድ ለዚሁ ጉዳይ ብቻ ተብሎ በተቋቋመ፣ በከፍተኛ ደረጃ ሀገራቸውንና ኅብረተሰቡን ባገለገሉና የመንፈስ ጥንካሬና ሥነ ምግባር ባላቸው ስመጥር ዜጎቿ "ሽማግሌዎች" በታነፀ ሸንጎ አማካይነት ነው። ይህም ሸንጎና ተግባሩ የመንግሥትን ይሁንታ ማግኘት ግድ ነው፣ የዕርቀ ሠላም ሂደቱም በወቅቱ ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖ መቅረብና በህዝቡም ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።

ሸንጎው ሁለት ዓላማዎች ይኖሩታል፤ አንደኛው ተጎድተናል ለሚሉትና ጎጂዎች ናቸው ለተባሉት ክፍሎች መወያያ መድረክ ፈጥሮ ማወያየት ነው። ሁለተኛው ወንጀል ተፈጽሟል ለሚባሉ ሁኔታዎች ሕጋዊ የሆነ የመጨረሻ ለችግሩ መቋጠሪያ የሚሆን ተቀባይነት ያለውና ቀጪ ብቻ ሳይሆን አስታራቂ የሆነ ብያኔ ማሳለፍ ነው። ይህ ታሪካዊ ክንዋኔም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሆን ከወዲሁ መስማማት አለብን።

<u>**ከዕርቀ ሠላም ሂደት የምንጠብቀው ምንድን ነው?**</u>

ከዚህ ሂደት የምንጠብቀው የተጎዱት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ችግሩ የተፈጠረበትን ሁኔታ ተገንዝበው፣ ይቅር ለእግዚአብሔር እንዲሉ፣ ጎጂዎቹ ይቅርታ እንዲጠይቁና በመካከላቸው ዕርቅ እንዲመጣ ነው። ከሕግ አንጻር የሚፈለገው ፍጹም የሆነ ፍትህ አይደለም፤ ከችግሩ ስፋትና የዘመን ርዝመት ምክንያት ሊገኝ የሚችለው የመቀጣጫ ፍትህ (retribution) ሳይሆን ወንጀሉ የተፈጸመበት ወገን ለጉዳቱ መደጎሚያ፣ የሚወደውን ላጣ ዕንባ ማድረቂያ ተምሣሌት ከጎጂው ወይም ከሸንጎው እንዲያገኝና (restitution and reconciliation) ዕርቀ ሠላም እንዲወርድ ነው።

<u>**የዕርቀ ሠላም ኺደቱ ከተሣካ የሚገኘው ሀገራዊ ጥቅም:-**</u>

- በኅብረተሰብ ደረጃ የመንፈስ መረጋጋት፣ ብሔራዊ/ሀገራዊ ሠላምና በተወሰኑ ቁም ነገሮች ላይ ሀገራዊ ስምምነት ማግኘት ነው። <u>**ሀገራዊ በሆነ የእርቅ ሂደት፣ በሀገራዊ የእርቅ ጉባዔ በታቀፈ ዴሞክራሲያዊ ውይይት፣ በሠላም፣ በዴሞክራሲ እና በአንድነት ሃሳቦች ላይ ስምምነት መፍጠር ብንችል በእውነት ታሪካዊ የሆነ ብሔራዊ ተሃድሶ ጀመርን ማለት ይሆናል።**</u>
- በግለሰብ ደረጃ በፍራቻ ቦታ ወኔና በራሱ እምነት ያለው፣ እርስ በርሱ የሚጠራጠር ሳይሆን የሚተማመን፣ ቅኝት ያጣ ሳይሆን ብሔራዊ ስሜቱ የጠራ ዜጋ ነው።
- በቡድን ደረጃ ደግሞ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁለት ዓቢይ ሁኔታዎች ከተፈጠሩና ከተገኙ፣ በሀገራችን ያሉትና የሚፈጠሩት ማኅበረሰባት የሚከባበሩና የሚደጋገፉ የሀገሪቱ አኩሪና አንጸባራቂ የባህልና የታሪክ ጌጦቿ መሠረት ይሆናሉ፣ እንዲሁም የተለያዩ ፖለቲካ ቡድኖች ቢያንስ የሚቻቻሉና የሚደማመጡ፣ የምርጫ ፖለቲካን ደንብና ውጤት የሚቀበሉ ይሆናሉ።
- ያኔ ያለ የሌለ ሀብታችን፣ የሰው የመንፈስና የጉልበት አቅም ተሰባስቦ ረሃብንና ችጋርን በአጭር ጊዜ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን ከማንም እኩል የምትበለጽግ ሀገራችንን በጋራና በኩራት እንገነባለን።